# ማውጫ

## ክፍል አንድ

1. መግቢያ...................................................................................................... 3
2. የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር አመሠራረት ................................................................... 3
3. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አላማ ............................................................................ 4
4. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር ................................................................ 4
5. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል .......................................... 5
6. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ ................................................................ 5
7. የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት እና አቅርቦት የሰራ ሂደት
መግለጫ (process description)........................................................................ 6
8. የኦዲቱ አላማ..................................................................................................8
9. የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ....................................................................................... 8
10.የኦዲቱ አካባቢ.................................................................................................. 9
11.የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ................................................................................ 9
12.የኦዲት መመዘኛ መስፈርት .................................................................................. 10

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

ሀ.ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ዉሀ ቢሮዎች በመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠናና ድጋፍ መስጠታቸውን እንዲሁም ከዉጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል ከተማ እና ወረዳዎች የሚተገበሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች ግንባታዎች በታያዘላቸው የግዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ መከታተላቸውንና መቆጣጠራቸውን በተመለከተ፦
13.ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ዉሀ ቢሮዎች ስለሚሰጡት ስልጠና በተመለከተ፤............ 12
14.ሚኒስተር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን መረጃ አጠናክሮ መያዙን እና ክልሎች መረጃውን ጥቅም ላይ ስለማዋላቸው፤ ........................................................................... 13
15.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርት በተመለከተ፤ ...................... 14
16.የno objectionን አሠራር፣ መመሪያ እና ስልጠናን በተመለከተ፤.................................. 14

17.ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ ገደብ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ................................ 15

18.በውሀ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በኩል የሚስተባበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ...................... 17

ለ.ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ውሀ ቢሮዎች ከዉጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል ከተማ እና ወረዳዎች የሚተገበሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸዉ በጀት ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን መከታተላቸውንና መቆጣጠራቸውን በተመለከተ፦

19.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራዎችን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን በተመለከተ ........................ 18

20.ክልሎች የተለቀቀላቸውን ገንዘብ ስለመጠቀማቸው እና ሚኒስተር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ሂሳብ አፈፃፀምን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን በተመለከተ፤ ...................... 20

21.ክልሎች ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት አገልግሎት ስለማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች እና ስለተቆፈሩ ጉድጓዶች መረጃ መያዛቸውን እና በመረጃው ላይ ተመስርተው የመፍትሄ እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ........................................ 22

ክፍል ሦስት

22.የመደምደሚያ ሀሳቦች ........................................................................................ 24

ክፍል አራት

23.የማሻሻያ ሀሳብ

24.አባሪ 1

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

የውሀና ኢነርጂ ሚኒስቴር አመሠራረት

1. የመጀመሪያው የውሀ ሀብት አስተዳደር አካል ከተመሰረተበት ከ1950ዎቹ አንስቶ የውሀው ክፍለ ኢኮኖሚ የተለያየ ቅርጽና ይዘት እየያዘ እስከ 1983 ደርሷል፡፡
2. በ1983 የፌደራል ስርአት መፈጠሩን ተከትሎ የውሀ ሀብት አስተዳደር በፌደራል እና በክልል ደረጃ ተዋቀረ፡፡ በዚሁ መሰረት የውሀ ሀብት ልማት እና አስተዳደር ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ በተቋቋመው የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሚኒስተር አንድ ዘርፍ ሆኖ ተቋቋመ፡፡
3. አገሪቱ ያላትን የከርሰ ምድር እና የገጸ ምድር ውሃን ታሳቢ በማድረግ ውሃ ትልቁ የሀገሪቷ ሃብት መሆኑ ስለታመነበት ባለስልጣኑ በ1987 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 4/87 የውሃ ሃብት ሚኒስቴር በመባል በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ ተቋቋመ፡፡
4. ቀደም ሲል በውሀው ዘርፍ ተቋቁመዉ ከነበሩ ባለስልጣን መ/ቤቶች ውስጥ የመጠጥ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የሚኒስቴር መ/ቤቱ አንድ መምሪያ ሆኖ ሲደራጅ የብሄራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ድርጅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ሆኖ እንደገና ተቋቋመ፡፡ በ1990 ዓ.ም የአዋሽ ተፋሰስ የውሀ ሀብት አስተዳደር ድርጅት ፣ በ1991 ዓ.ም ደግሞ የውሀ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ሲመሰረቱ የውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በ1991 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለውሀ ሀብት ሚኒስቴር በመሆን ተደራጅቷል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ተቋሞች በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 268/94 የውሀ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለውሀ ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆኖ በከተሞች መጠጥ ውሀና በመስኖ መስክ ፋይናንስ የማሰባሰብ፣ የማቅረብና የማበደር ተግባርን እንዲያከናውን ተቋቁሟል፡፡
5. አብረው ሊሰሩና ሊመጋገቡ የሚችሉ ሥራዎች ለማገናኘት በ2003 ዓ.ም. በተሰራው አዲስ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አደረጃጀት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 691/03 አማካኝነት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተብሎ ተቋቁሟል፡፡

## የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አላማ

6.የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አላማ የሀገሪቱ የውሀ ሀብት በአግባቡ ተጠብቆ ለኢትዮጲያ ህዝብ ለላቀ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መዋሉን፣ በሚገባ መጠበቁን መከታተልና መቆጣጠር፣ የውሀ ጎጂ ገጽታዎችን መከላከል እንዲሁም የውሀ ሀብት ጠቅላላ አስተዳደር በሚገባ መካሄዱን ማረጋገጥ ነው፡፡

## የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

7.የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች አሉት፡-

- የውሃ ሀብትና የኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
- የተፋሰስ ጥናት በማካሄድ የሀገሪቱን የከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የውሃ ሀብት አለኝታ በመጠንና በጥራት ይለያል፤ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ከአንድ በላይ የሆኑ ክልሎችን አቋርጦ የሚፈስ ወይም የሚያዋስን ውሃ በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶችና በክልሎች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ይወስናል፤
- በወሰንና ወሰን ተሻጋሪ የውሃ አካላት አጠቃቀም ላይ ጥናት ያካሂዳል፤ አለም አቀፍ ውሎችን ይደራደራል፤ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
- ለሚመለከታቸው ሌሎች አካላት እንዲተላለፉ ካልተደረገ በስተቀር፤ በፌዴራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችንና የውሃ ውቅሮችን ያስተዳድራል፤
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች የሚውል ውሃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤
- የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ ያደርጋል፤ ከውጭ በሚገኝ ዕርዳታና ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤


## የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ሀይል

8.የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሆኖ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ተዋቅሯል፡፡በውሃው ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ስር 6 ዳይሬክቶሬቶች፣ በኢነርጂው ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ስር 6 ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም 13 ድጋፍ ሰጭ ዳይሬክቶሬትና 3 ጽ/ቤቶችን ይዟል፡፡ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላላው 1288 እንዲሁም ለውሀ እና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት 26 የሰው ሀይል እንዲኖር የተፈቀደ ቢሆንም ሚኒስትሩንና ሚኒስትር ዴኤታዎቹን ጨምሮ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጠቅላላ በስራ ላይ ያለው የሰው ሀይል 951 ሲሆን በውሀ እና ሳኒቴሽን ዳይሬክቶሬት ደግሞ 24 የሰው ሀይል ይገኛል፡፡

## የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ

9. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስራውን የሚያከናውነው በመንግስት በሚመደብለት በጀት ሲሆን በ 2001፤ በ 2002 እና በ 2003 በጀት ዓመታት እንደየቅደም ተከተሉ ከመንግስት የተመደበለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት ብር 1,034,296,149.፣ 1,502,543,010. እና ብር 1,990,216,275. ሲሆን ከዚህ ውስጥ በ 2001 በጀት ዓመት ብር 1,013,360,777.፣ በ 2002 ብር 471,180,221. እንዲሁም በ 2003 በጀት አመት 1,940,080,373 ስራ ላይ አውሏል፡፡

# የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት እና አቅርቦት የስራ ሂደት መግለጫ (process description)




ማሳሰቢያ፦ በ { } ምልክት ውስጥ ያለው የስራ ፍሰት በክልሎች የሚሰራ ሲሆን ቀሪው በሚኒስተር መ/ቤቱ የሚሰራ ነው።

- ከላይ ከቀረበው የሰንጠረዥ መግለጫ በተጨማሪ የውሀ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት በከተሞች መጠጥ ውሀ አቅርቦት መስክ ፋይናንስ የማሰባሰብና የማበደር ተግባርን ያከናውናል።

## ፅሁፋዊ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት እና አቅርቦት የስራ ሂደት

### መግለጫ (process description)

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለመስጠት በመጀመሪያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍላጎት የመነጩ እቅዶች/ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ረቂቅ እቅድ አዘጋጅቶና በረቂቅ እቅዱ ላይ አስተያየት እና ማሻሻያዎችን አካቶ በመ/ቤት ደረጃ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እቅድ ካዘጋጀ በኋላ ክልሎች ፕሮፖዛል እንዲያቀርቡ ጥሪ ያቀርባል።በቀረበላቸው ጥሪ መሰረት ክልሎች ፕሮፖዛል ካላቀረቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በራሱ የሚያቀርብበትን አማራጭ ይፈልጋል። ክልሎች ጥሪውን ተከትለው ፕሮፖዛሎችን ካቀረቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፕሮፖዛሎቹን ይከልሳል።ፕሮፖዛሎቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት ሳያገኙ ከቀሩ ለክልሎቹ መመለስ እንዲሁም ተቀባይነት ካገኙ ለፕሮፖዛሎቹ ቅደም ተከተል መስጠት ፣በቅደም ተከተላቸው መሰረት ፋይናንሰሮችን ለይቶ ማሳመን፣ፕሮፖዛሎቹን ለፋይናንሰሮች ማቅረብ እና የውል ሰነድ በማዘጋጀት ስምምነት መፈራረምን ያከናውናል። ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለፕግራሞቹ/ፕሮጀክቶቹ ፈንድ በወቅቱ ማስለቀቅ፣በቴክኒካልና ፋይናንሻል አፈጻጸም ዙሪያ ድጋፍ መስጠት፣ለአፈፃፀም የሚረዱ መመሪያና ደንቦችን ማዘጋጀት እና አፈጻጸማቸውን መከታተል፣የቴክኒክ ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን እንዲሁም ከስራው ጋር አግባብነት ያላቸውን አካላትን በማስተባበር የፕሮግራሞቹን/ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ያግዛል። የስራዎችን መገባደድ ተከትሎም የማጠቃለያ ሪፖርት ያዘጋጃል።

11. ክልሎች በበኩላቸው የመጠጥ ውሀ አቅርቦትን ለህብረተሰቡ ለማድረስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቀባይነት ላገኙ ፕሮፖዛሎች ጥናትና ዲዛይን መስራት፣ለፕሮጀክቶች ግንባታና አስተዳደር ጥናት እና ዲዛይን ማከናወን፣ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶቹ የሚገነቡበት ንጹህ የመጠጥ ውሀ ምንጭ ከከርሰ ምድር እና ገፀ ምድር መምረጥ፣ በፕሮጀክቶች ጥናት መሰረት ለግንባታ የስራ መግለጫ (term of reference) ማዘጋጀት፣ አማካሪ/ኮንትራክተር መቅጠር ፣የፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ፣ግንባታዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ርክክብ መፈፀም እንዲሁም ግንባታዎች አገልግሎት ላይ ከዋሉ በኋላ የኦፐሬሽን እና ጥገና ስራ፣ የውሀ ጥራት እና ቁጥጥር እንዲሁም የሲቪልና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራ በማከናወን ፕሮጀክቶችን ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል።

## የኦዲቱ አላማ

12.የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ለመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት የሚደረገው ድጋፍና ክትትል በአግባቡ መተግበሩን እንዲሁም የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት አስፈፃሚ ባለድርሻ አካላቶች በቅንጅት መስራታቸውን በማየት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የገንዘብ መጠንና የግዜ ገደብ መግንባታቸውን እንዲሁም ቀጣይነት ያለው የመጠጥ ውሀ አቅርቦት መስጠታቸውን ማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ በክልሎች እና በባለድርሻ አካላት የሚከናወኑ የመጠጥ ዉሀ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች ወጪ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋ እና ዉጤታማ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ሊያደርጉ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው ፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

13.ኦዲቱ የሸፈነው በሦስት በጀት ዓመታት ማለትም ከ2001 በጀት ዓመት እስከ 2003 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት አፈፃጸም እና ውጤታማነትን ለማሳካት የተዘረጋውን የአሠራር ስርዐትን እና የተሠሩ ሥራዎችን በመገምገም ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በውሀ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሲሆን በናሙና በተመረጡ የክልል ውሀ እና ኢነርጂ ቢሮዎች፣ በወረዳ እና ከተሞች ካሉ የውሀ ሀብት ፅ/ቤቶች ማስረጃዎችን በመከለስ፣ ግንባታዎችን በመመልከት ለሚመለከታቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ እና ወረዳ የመጠጥ ውሀ ጽ/ቤት የሥራ ሀላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ እና የተገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን በአካል ተገኝቶ በመመልከት ነው፡፡

14.በዚህም መሠረት በውጭ ድጋፍ እና እርዳታ በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ እንዲሁም በክልሎች ተግባራዊ የሚደረጉ የመጠጥ ውሀ ፕሮግራሞችን ከሚተገብሩ ዘጠኝ ክልሎች እና 458 ወረዳዎች ውስጥ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የውሀ እና ኢነርጂ ቢሮ ፣ ለጎንደር ከተማ የመጠጥ ውሀ አገልግሎት ድርጅት፣በጎንደር እና ባህርዳር ከተማ ዙሪያ ለሚገኙ 4 የወረዳ የመጠጥ ዉሀ ጽ/ቤት የስራ ሀላፊዎች፣ በሐረሪ ክልላዊ መንግስት የውሀ እና ኢነርጂ ቢሮ የሥራ ሀላፊዎች ፣በሀረሪ ክልል ዙሪያ ለሚገኙ 2 የወረዳ የመጠጥ ውሀ ፅ/ቤት የሥራ ሀላፊዎች፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የውሀ እና

ኢነርጂ ቢሮ የሥራ ሀላፊዎች ፣በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ለሚገኙ 2 የወረዳ የመጠጥ ውሀ ፅ/ቤት የሥራ ሀላፊዎች ፣ለሀዋሳ ውሀ እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት የሥራ ሀላፊዎች ፣ ለቡታጅራ ከተማ ውሀ እና ፍሳሽ አገልግሎት የሥራ ሀላፊዎች፣ ለኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የውሀ እና ኢነርጂ ቢሮ የሥራ ሀላፊዎች፣ ለሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የውሀ እና ኢነርጂ የስራ ሀላፊዎች፣ ለውሀ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት የሥራ ሀላፊዎች ፣ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ሀላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ማስረጃዎችን በመከለስ እንዲሁም በጎንደር እና ባህርዳር ከተማ ዙሪያ በሚገኙ 4 ወረዳዎች ፣ በሀረሪ ክልል ዙሪያ በሚገኙ 3 ወረዳዎች እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በሚገኙ 2 ወረዳዎች በአካል ተገኝቶ በወረዳዎቹ የተገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን በመመልከት እና ማስረጃ በመተንተን ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የኦዲቱ አካባቢ

15.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ በውጪ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም ቀልጣፋነት እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ የሚል የኦዲት አካባቢን ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

16.ከላይ በተመረጠው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተለዩ ሲሆን ለአንደኛው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ 4 ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ተቀምጠውለታል፡፡ በዚሁም መሠረት የተለዩት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

1.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል ከተማዎች እና ወረዳዎች የሚከናወኑ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮግራሞች ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ ማቀዱን፣ መከታተሉን፣መቆጣጠሩን እና ማስተባበሩን ማረጋገጥ።

1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን ለሚተገብሩ ክልሎች ፣ ከተማዎች እና ወረዳዎች ፕሮጀክቶችን ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ እንዲፈጽሙ በስልጠና፣በቴክኒክ ድጋፍ እና በእቅድ አፈፃጸም ዙሪያ በቂ እገዛ ማድረጉን ማረጋገጥ።

1.2 በወረዳዎች የሚተገብሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የንፁህ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ግንባታ በታቀደላቸው ገንዘብ እና ግዜ መፈፀማቸውን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን ማረጋገጥ።

1.3 በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ እና ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ድጋፍ የሚከናወኑ የመጠጥ ውሀ ፕሮግራሞችን /ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የሚያደርጉ ክልሎች ፕሮጀክቶችን ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በታቀደላቸው ገንዘብ እና ግዜ መፈጸማቸዉን ማረጋገጥ።

1.4 በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ እና ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ድጋፍ የሚከናወኑ የንፁህ መጠጥ ውሀ ፕሮግራሞችን /ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ክልሎች ፕሮጀክቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ቀጣይነት ያለው አቅርቦት/አገልግሎት/ እንዲሰጡ መከታተላቸውን እና መቆጣጠራቸውን ማረጋገጥ

2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት/ፕሮግራሞችን ተፈፃሚ ከሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እና የፍላጎት ጥናት ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17.በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሁለት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች እና አራት የኦዲት ንኡስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 33 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

(Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል። የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሻሻለው አዋጅ፣ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት(BPR document)፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች፣ የፕሮጀክቶች አፈፃጸም ማንዋል፣የ project status report፣ የwash monitoring & evaluation manual እንዲሁም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ለባለድርሻ አካላት የቀረቡ መጠይቆች እና የተከለሱ ማስረጃዎች ናቸው።በተዘጋጁትም የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### ሀ.ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ዉሀ ቢሮዎች በመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠናና ድጋፍ መስጠታቸውን እንዲሁም ከዉጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል ከተማ እና ወረዳዎች የሚተገበሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች ግንባታዎች በታያዘላቸው የግዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ መከታተላቸውንና መቆጣጠራቸውን በተመለከተ፦

### ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ዉሀ ቢሮዎች የሚሰጡትን ስልጠና በተመለከተ፤

18.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ዉሀ ቢሮዎች እና ከተማ ዉሀ አገልግሎቶች በመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክት ግንባታ፤ የግዢ ጨረታ ሰነድ አዘገጃጀት እንዲሁም በግዢ አፈፃፀም ዙሪያ ፍላጎትን መሰረት አደርጎ ስልጠና ሊሰጥ እና ሥልጠናዎች ያስገኙትን ጠቀሜታ (Training Impact Assessment) በየጊዜው ሊለካ ይገባዋል፡፡እንዲሁም የክልል ውሀ ቢሮዎች በመጠጥ ውሀ ፕጀክቶች ግንባታ፣የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ተገንብተው የተበላሹ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች እድሳት እና ሌሎች ከመጠጥ ውሀ ግንባታ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለወረዳ ውሀ ፅ/ቤቶች እና የከተማ ውሀ አግልግሎቶች ስልጠና መስጠት ይገባቸዋል፡፡

19.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ውሃ ቢሮዎች እና የከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ፈንድ በሚሰጡ ባንኮች የግዥ ስርዕት እና በ LC አከፋፈት ዙሪያ በቂ ስልጠና ያልሰጠ ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለተግባሪ አካላት የሚሰጡ ሥልጠናዎች ያስገኙት ጠቀሜታም በየጊዜው እንደማይለካ ታውቋል፡፡

20.በዚህ ዙሪያ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአቅም ግምገማ /capacity assessment/ እንደሚሰራ እና በዚሁም መሰረት ለአራት ክልሎች የ “no objection” ውክልና እንደተሰጠ ገልፀዋል፡፡

21.ከላይ በተጠቀሱት ርእሶች ዙሪያ በቂ ስልጠና አለመሰጠቱ ለno objection ዝግጅት እና ምላሽ የሚፈጀው ጊዜ እንዲራዘም እንዲሁም የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከተያዘላቸው ጊዜ በላይ

እንዲሄዱ የሚያደርግ ሲሆን የተሰጡ ስልጠናዎች ያስገኙት ጠቀሜታም ባለመለካቱ የስልጠናዎችን ውጤታማነት እና ሰልጣኞች ያገኙትን ክህሎት እናዳይለካ አድርጓል፡፡

22.በኦዲቱ ወቅት ከታዩ እና በIDA/DFID/ADB ከታቀፉ ሰባት ወረዳዎች ውስጥ የላይ አርማጭ፣ሜጫ፣ዳንግላ፣ጃቢ ጠናን እና መስቃን ወረዳዎች በመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታ እና ጥገና ከክልሎች ስልጠና እንዳልተሠጣቸው የታወቀ ሲሆን የቡታጅራ ውሃ አቅርቦት እና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ስልጠና እንዲሰጠው እና ድጋፍ እንዲደረግለት በተደጋጋሚ የክልል ውሃ ቢሮዉን እገዛ ቢጠይቅም ምላሽ እንዳላገኘ ታውቋል፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን መረጃ አጠናክሮ መያዙን እና ክልሎች መረጃውን ጥቅም ላይ ማዋላቸውን በተመለከተ፤

23.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን መረጃ አጠናክሮ በየአመቱ ወቅታዊ ሊያደርግ እና የክልል ውሀ ቢሮዎች ለግንባታ ጨረታ በሚያወዳድሩበት ጊዜ በሚንስቴር መ/ቤቱ የተጠናከረዉን የኮንትራክተሮች መረጃ መሰረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

24.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንትራክተሮችን መረጃ አጠናክሮ የማይዝ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

25.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎች የኮንትራክተሮችን ብቃት እና አቅምን የሚያዩበት የተጠናቀረ መረጃ ባለመያዙ ኮንትራክተሮች አስቀድመው የጀመሯቸውን ስራ ሳይጨርሱ እና በቂ አቅም ሳይኖራቸው እንዲሁም የቅርብ ግዜ የመልካም ስራ አፈፃፀማቸው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይረጋገጥ አዲስ ጨረታ ተወዳድረው ካሸነፉ በኋላ እስከ አምስት ወር ድረስ ስራ ሳይጀምሩ እንደሚቆዩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

26.ይህንን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሀላፊዎች ተጠይቀው እስከ አሁን በዚህ ዙሪያ የተሰራ ስራ የሌለ መሆኑን ነገር ግን ወደፊት በዚህ ዙሪያ ለመስራት ማቀዳቸዉን ገልጸዋል ፡፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለሚያዘጋጀው የእቅድ ክንውን ሪፖርት በተመለከተ፤

27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ውስጥ በአፈፃፀም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡

28. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2002 እና በ2003 አዘጋጅቶ ለተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የካፒታልና የመደበኛ ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ውስጥ በሠንጠረዥ 1፣2 እና 3 ላይ ስለተመለከተው፣ ስለግንባታዎች መዘግየትና የፋይናንስ አጠቃቀም ዝቅተኛ ስለመሆኑ አላካተተም፡፡

29. ስለጉዳዩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቂ ምላሽ አልሰጡም፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀዉ የካፒታል እና የመደበኛ ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በWaSH የመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና አቅርቦት ዙሪያ ያጋጠሙ የግንባታ መዘግየቶችን እና የፋይናንስ አጠቃቀም ዝቅተኝነትን ባለማካተቱ የሪፖርቱ ተጠቃሚ የተሟላ መረጃ እንዳያገኝ የሚያደርግ እና ተጠያቂነትን እንዳይጠናከር የሚያደርግ ነው፡፡

## የno objectionን አሠራር፣ መመሪያ እና ስልጠናን በተመለከተ፤

30. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውክልና ለሰጣቸው ክልሎች የ"no objection" ምላሽ ሲሰጡ የሚጠቀሙበት መመሪያ ሊያዘጋጅ፣በ "no objection" አሰጣጥ ዙሪያ ለክልሎች ስልጠና ሊሰጥ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የ "no objection" መልስ የሚሰጥበት የግዜ ገድብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. የno objection ጥያቄ በ15 ቀን ዉስጥ ምላሽ ማግኘት ሲገባዉ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው በአንዳንዶቹ ክልሎች ከ 1 ወር እስከ 11 ወር ድረስ የዘገዩ ምላሾች መኖራቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ውሃ ቢሮዎች እና ለከተማ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎቶች ፈንድ በሚሰጡ ባንኮች የግዥ ስርዕት ዙሪያ በቂ ስልጠና እንዳልሰጠ ታውቋል፡፡

32.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የከተማ ውሀ አገልግሎቶች ውስጥ የቡታጅራ እና ሀዋሳ ከተማ ውሀ አገልግሎት ድርጅቶች ለጠየቁት “no objection” ምላሽ ለማግኘት እስከ 4 ወር ድረስ የዘገየባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

33.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በባንኮች የግዥ ስርዐት ዙሪያ ተከታታይ ስልጠና ባለመስጠቱ የክልል ውሀ ቢሮዎች እና የከተማ ውሀ አገልግሎቶች የ “no objection” ፍቃድ ከሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ፈንድ ከሚሰጡ ባንኮች ሲጠይቁ ተደጋጋሚ ምልልስ እንዳለ ታውቋል፡፡በኦዲቱ ወቅት ከታዩት ክልሎች ውስጥ በአማራ ክልል በ18 ወር ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብለው ለታሰቡ ፕሮጀክቶች የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ለማካሄድ ለጨረታ ዶክመንት ዝግጅት እና ለጨረታ ዶክመንት ምዘና ሪፖርት የ “no objection” ፍቃድ ተጠይቆ ምላሽ የተገኘው ከ11 ወር በኂላ እንደሆነ ታውቋል፡፡

34.ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በባንኮች የግገር ስርአት ዙሪያ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን ግን ገልፀዋል፡፡

## ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ ገደብ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ

35.በውጪ እርዳታ/ብድር የሚደገፉ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ግንባታዎች በተያዘላቸው የግዜ ገደብ ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

36.በ IDA/DFID እና ADB ድጋፍ ሊሰሩ ከታሳቡ አነስተኛ እና በአንፃራዊ ብዙ ገንዘብ የማይጠይቁ እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ከሚተገበሩ የመጠጥ ውሃ ስራዎች ውስጥ ከ 2002-2003 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊተገበሩ ታስበው ከነበሩት 3926 ምንጭ ማጎልበት (spot spring) የውሃ ስራዎች ውስጥ የተሰሩት 2549 (66%) ሲሆን በሁለት አመት ሊተገበሩ ከታሰቡት 3567 የእጅ ጉድጓዶች (Hand dug wells) ውስጥ የተሰሩት 2091(58%)ናቸዉ፡፡

37.ከፍያለ ካፒታል በሚጠይቁ እና ብዙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ከሚያደርጉ የገጠር የመጠጥ ውሃ ስራዎች ውስጥ ከ 2002-2003 ሊገነቡ ከታሰቡ 2345 ጥልቅ ጉድጓዶች (Shallow Well, Deep Wells) ውስጥ የተሰሩት 1161(49.5%) ሲሆን በነዚህ አመት ውሰጥ ይገነባሉ ተብለው ከታሰቡት 576 /የገጠር ቧንቧ ዝርጋታ/ rular pipe system (RPS) ውስጥ ተሰርተው የተገኙት 103 (18%) ብቻ ናቸው፡፡

38.በ2003 ዓ.ም በድሬድዋ እና ሱማሌ ብሄራዊ ክልል በአጠቃላይ በወረዳ ደረጃ  በ IDA/DFID እና ADB ድጋፍ አማካኝነት ሊተገበሩ ታስበው የነበሩ 24 የመጠጥ ውሃ ስራዎች ቢሆኑም በበጀት አመቱ በሁለቱም ክልሎች ምንም አይነት ግንባታ እና ጥገና አልተካሄደም፡፡

39.በጎንደር ከተማ እየተገነባ ያለው የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፤ ውሃ የሚወጣበት ቦታ መረጣ ላይ በነበረ ችግር ፤በዲዛይን ለውጥ እና በጉድጓድ ቆፋሪ ድርጅቶች /drilling companies/ አለመኖር ስራው በመዘግየቱ መጀመሪያ ስራውን ለመጨረስ በዕቅድ ከተያዘው በላይ ተጨማሪ በጀት እስከ ብር 200,000,000. እንደጠየቀና  ከፍተኛ የበጀት እጥረት እንዳጋጠመው ታውቋል፡፡

40.በዚህ ዙሪያ የክልል ውሀ ቢሮ እና የወረዳ ውሀ ፅ/ቤት ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በፕሮግራሞቹ የተያዙ ግንባታዎች በእቅድ መሰረት ያልተገነቡበት ምክንያቶች የአስፈፃሚዎች አቅም ማነስ፣ ለአንድ ስራ የሚጠየቁ no objectionኖች እና የሚፈጁት ግዜ ከፍተኛ መሆን እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

41.ከላይ ከተገለፀት ምክንያቶች በተጨማሪ  የክልል ውሀ ቢሮ እና የወረዳ ውሀ ፅ/ቤት  ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ  በፕሮግራሞቹ የተያዙ ግንባታዎች በእቅድ መሰረት ካልተገነቡበት ምክንያቶች ውስጥ የበጀት በወቅቱ አለመለቀቅ አንዱ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ክልሎች በጀት ሲለቁ እንደሚያዘገዩ የታወቀ ሲሆን፤ከታዩት የወረዳ ውሀ ፅ/ቤቶች ውስጥ የሶፊ፣ድሬ ጠያራ፣ላይ አርማጮ፣ጃቢ ጠናን፣ሜጫ እና ዳንግላ ወረዳዎች በጀት ከክልሎቹ በወቅቱ እንዳልተለቀቀላቸው ታውቋል፡፡

42.ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ግዜ ባለመጠናቀቃቸው ሚኒስተር መ/ቤቱ እና የክልል ውሀ ቢሮዎች በIDA/DFID,ADB እና በአውሮፓ ህብረት በሚደገፉ ፕሮግራሞች በከተማ እና ገጠር በሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች 9,250,000 ህብረተሰብን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅደው የነበረ ቢሆንም ፕሮግራሞቹ ሊጠናቀቁ ከ1 አመት እስከ 1 አመት ተኩል ብቻ እየቀራቸው (ለፕሮግራሞቹ ከተያዘው ግዜ ከ75-94% ካለቀ በኋላ) ተጠቃሚ ያደረጉት ህብረተሰብ 3,888,900 (42 %) ብቻ እንዲሆን አድርጓል፡፡

## በውሀ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በኩል የሚስተባበሩ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ

43.በውጪ እርዳታ/ብድር የሚደገፉ እና በውሀ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በኩል የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ እና የገንዘብ በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡

44.የውሃ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በአጠቃላይ ከሚያገኘው ፈንድ ውስጥ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ ከ30% በላይ ተጠቅሞ የማውያቅ ሲሆን በ2003 በጀት አመት የተጠቀመው 51% ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡

45.በፅ/ቤቱ ከሚስተባበሩ የከተማ የመጠጥ ፕሮጀክቶች ውስጥ የተጠናቀቁት የሚዛን ተፈሪ፣ የወልቂጤ ፣የሃዋሳ እና አክሱም ከተማ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ እነዚህም ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁት እያንዳዳቸው ከአንድ አመት በላይ ዘግይተው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

46.በፅ/ቤቱ ከሚያስተባብሩት የከተማ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ የሀረሪ እና የክብረመንግስት ከተሞች ስራቸው እስከ መስከረም 2004 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ያልተጠናቀቀ ሲሆን መጠናቀቅ ከነበረባቸው ጊዜ በላይ 6 እና 4 አመት እንደየቅደመ ተከተላቸው መዘግየታቸው ታውቋል፡፡የሀረር ከተማ ፕሮጀክት ከላይ በተጠቀሰው ግዜ መስጠት ከነበረበት የመጠጥ ውሀ ውስጥ የሚሰጠው ከ 50-60% ብቻ እንደነበር ታውቋል፡፡

47.ይህንን በተመለከተ የፅ/ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ችግሮቹ እንዳሉ እና ለችግሮች የሚጠቀሱ ምክንያቶችም የno objection መዘግየት፣የኮንትራክተሮች እና እቃ አቅራቢዎች ስራቸውን በአግባቡ አለመስራት፣ስራውን ለመስራት ያሸነፉ ኮንትራክተሮች ስራቸውን በተያዘላቸው ግዜ አጠናቀው ክፍያ አለመጠየቅ ፣ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ግዜ ባለመጠናቀቃቸው ከታሰበው/ከታቀደው ውጪ ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ወጪያቸው መጨመር እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

48. በሀረር እና ክብረመንግስት የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች መዘግየት ዙሪያ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው ፕሮጀክቶቹ ከላይ በተገለፀው መሰረት የዘገዩ መሆኑን ገልፀው የሀረር የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት በ2003 ዓ.ም አገልግሎት መስጠት

እንደጀመረ እና የክብረመንግስት የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት በመጋቢት 2004 እንደሚጠናቀቅ ገልፀዋል፡፡

49.የግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቅ በእቅዱ መሰረት ተጠቃሚ ሊሆን የታሰበው ህብረተሰብ በወቅቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርጓል፡

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና የክልል ውሀ ቢሮዎች ከዉጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል ከተማ እና ወረዳዎች የሚተገበሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸዉ በጀት ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈፀማቸውን መከታተላቸውንና መቆጣጠራቸውን በተመለከተ፦

## ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራዎችን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን በተመለከተ

50.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ከተሞች/ወረዳዎች የሚከናወኑ የመጠጥ ውሀ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በክልሎች በሚጠናከር ሪፖርት እና በአካል ጉብኝት በማድረግ መከታተል፣መቆጣጠር እና ድጋፍ መስጠት ይገበዋል፡፡

51.በአለም ባንክ ድጋፍ በሃዋሳ ከተማ በ 23,299,981. ብር ወጪ የተገነባው እና የካቲት 2003 ላይ የተጠናቀቀው ፕሮጀክት በሰከንድ 55 ሊትር ውሀ ለመስጠጥ እና ለ 24 ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የነበረ ቢሆንም በኦሮሚያ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰብ እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስቶች መካከል በተፈጠረው አለመግባባት እስከ 30/03/04 ድረስ ጥቅም እየሰጠ እንዳልሆነ ታውቋል፡፡(ፎቶ ግራፍ 1 እና 2)

52.በዚህ ዙሪያ የከተማው ውሀ ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ተጠይቆ ጉዳዩን ለሚኒስተር መ/ቤቱ ሪፖርት እንዳደረገ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ኮሚቴ ተቋቁሞ የነበረ ቢሆንም ኮሚቴው ችግሩን ሳይቀረፍ መቅረቱን ገልፀዋል፡፡

53.ከላይ የተጠቀሰው ፕሮጀክት ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ባለመዋሉ እስከ 30/03/04 ድረስ ሊሰጥ ይችል የነበረውን 1,283,040,000 ሊትር ውሀ ሳይሰጥ እንዲቀር እና የከተማው የመጠጥ ውሀ ሽፋን ከ55 % በላይ እንዳይዘል አድርጓል፡፡

54.ይህን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው ችግሩ እንደነበረ ሆኖም  አሁን መፍትሄ አግኝቶ ፕሮጀክቱ አገልግሎት ለመስጠት በዝግጅት ላይ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡



ፎቶ ግራፍ ቁጥር 1. ከላይ ለተገለፀው ፕሮጀክት ለ9.3 ኪሎ ሜትር የተዘረጋ የግፊት መስመር ቧንቧ



ፎቶ ግራፍ ቁጥር 2. ከላይ ለተገለጸው ፕሮጀክት የተሰራ 1,000,000 ሊትር ውሀ የሚይዝ የውሀ ታንከር

**ክልሎች የተለቀቀላቸውን ገንዘብ ስለመጠቀማቸው እና ሚኒስተር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ሂሳብ አፈፃጸምን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን በተመለከተ፤**

55.ክልሎች በ channel 1 ወይም channel 2 የሚለቀቅላቸውን የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ፈንድ/ገንዘብ በእቅዳቸው መሰረት ሊጠቀሙ እና ሚኒስተር መ/ቤቱ በውጪ እርዳታ/ድጋፍ የሚሰሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ሂሳብ አፈፃጸምን በየአመቱ በተዘጋጁት እቅዶች እና በ የ 4 ወሩ ከክልሎች በሚላክ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት መሰረት መከታተል እና መቆጣጠር ይገባዋል፡፡

56.የምንዛሪ ጭማሪን አካቶ በጠቅላላ ለ IDA/DFID ከተያዘው 3,402,568,612. ብር ውስጥ ፕሮግራሙ ከተጀመረ ከ 6 አመት ተኩል በኃላ እና ለመጠናቀቅ አንድ አመት ተኩል /19%/ ሲቀረው ስራ ላይ የዋለው ብር 1,177,620,534.(34.6%) ብቻ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 1 ቀርቧል/

/ሠንጠረዥ 1/

በIDA/DFID ድጋፍ የሚተገበረው የመጠጥ ውሃ ፕሮግራም አጠቃላይ የፋይናንስ አጠቃቀም

| አጠቃላይ በጀት | ለፕሮግራሙ የተያዘው ግዜ በአመት | በ 2003 በጀት አመት መጨረሻ ፕሮጀክቱ ለመጠናቀቅ የቀረው ግዜ | | እስከ 2003 አመት ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በአመት | በመቶኛ% (ከአጠቃላይ የፕሮግራሙ ግዜ ጋር በንፅፅር) | በገንዘብ | በመቶኛ% (ከአጠቃላይ የፕሮግራሙ በጀት ጋር በንፅፅር) |
| (A) | (B) | (C) | (D=C/B) | (E) | (F=E/A) |
| 3,402,568,612 | 8 | 1.5 | 19% | 1,177,620,534 | 34.6% |

57.በ 2003 በጀት አመት በአጠቃላይ ከ 2002 የተላለፈ እና የምንዛሬ ጭማሪን አካቶ ለክልሎች ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እና መከታትያ እንዲዉል በIDA/DFID ከተለቀቀ 1,199,216,827 ብር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው 372,460,910 (31%) ብቻ ነው፡፡/ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 2 ቀርቧል/

ሠንጠረዥ 2

በIDA/DFID ድጋፍ የሚተገበረው የመጠጥ ውሃ ፕሮግራም የ2003 በጀት አመት የፋይናንስ አጠቃቀም

| ለ2003 ዓ.ም የተፈቀደ በጀት (A) | በበጀት አመቱ የተለቀቀ፣ ከ2002 ዓ.ም የዞረ እና በምንዛሪ ጭማሪ የተገኘ አጠቃላይ ገንዘብ (B) | በበጀት አመቱ ጥቅም ላይ የዋለ | | ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ከተፈቀደው በጀት ጋር በንፅፅር (E=C/A) |
|---|---|---|---|---|
| | | በገንዘብ (C) | በመቶኛ % (በበጀት አመቱ ከተለቀቀ፣ከ2002 ዓ.ም የዞረ እና በምንዛሪ ጭማሪ ከተገኘ አጠቃላይ ሂሳብ ጋር በንፅፅር) (D=C/B) | |
| 1,669,907,904 | 1,199,216,827 | 372,460,910 | 31% | 22% |

58.በ ADB የሚደገፈው የንፁህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት መጀመሪያ እንዲጠናቀቅ ታሰቦ የነበረው በ 4 አመት ውስጥ ቢሆንም በዋጋ ንረት እና በተለየዩ ምክንያቶች ወደ 6 አመት ተራዝሟል፡፡ ለፕሮጀክቱ በምንዛሬ ጭማሪ የተገኘውን አካቶ ካለው አጠቃላይ ብር 1,013,452,115 በጀት ውስጥ ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከ 4 አመት ተከ ል በኃላ (ለፕሮጀክቱ ከተያዘው ጊዜ ውስጥ 25% እቀረው) ጥቅም ላይ የዋለው ገንዘብ ብር 213,412,588 (21%) ብቻ ነው፡፡ /ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 3 ቀርቧል/

በADB ድጋፍ የሚተገበረው የመጠጥ ውሃ ፕሮግራም አጠቃላይ የፋይናንስ አጠቃቀም

| አጠቃላይ በጀት (A) | እስከ 2003 በጀት አመት ድረስ የተለቀቀ ገንዘብ (B) | ለፕሮግራሙ የተያዘው ግዜ በአመት (C) | በ 2003 በጀት አመት መጨረሻ ፕሮጀክቱ ለመጠናቀቅ የቀረው ግዜ | | እስከ 2003 አመት ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | | ጥቅም ላይ የዋለው በጀት ከአጠቃላይ የፕሮግራሙ በጀት ጋር በንፅፅር (H=F/A) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በአመት (D) | በመቶኛ% (ከአጠቃላይ የፕሮግራሙ ግዜ ጋር በንፅፅር) (E=D/C) | በገንዘብ (F) | በመቶኛ% (እስከ 2003 በጀት አመት ድረስ ከተለቀቀ ገንዘብ ጋር ሲነፃፀር (G=F/B) | |
| 1,013,452,115 | 604,608,755 | 6 | 1.5 | 25% | 213,412,588 | 35.3 % | 21 % |

59.የADB ፕሮግራሙ ከተያዘለት 6 አመት ውስጥ አንድ አመት ተኩል እየቀረው የትግራይ፣አማራ፣ኦሮሚያ፣እና ደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ክልሎች እንደ ቅደም ተከተላቸው በአጠቃላይ ለፕሮግራሙ ከተያዘላቸው ብር 73,499,591፣ 231,868,151,፣ 333,140,774 እና 193,488,402 በጀት ውስጥ የተጠቀሙት ብር 20,596,575 (28)%፣ 38,308,867 (16%)፣ 82,748,267 (25%) እና 39,257,826 (20%) ብቻ ሲሆን ከአራቱ ልዩ ድጋፍ ከሚሹ ክልሎች ውስጥ የአፋር እና የሱማሌ ክልሎች እንደየቅደም ተከተላቸው ካላቸው 35,584,736 እና 78,164,185 ብር በጀት ውስጥ ጥቅም ላይ ያዋሉት ብር 4,857,091 (14%) እና 5,307,726 (7%) ብቻ ነው፡፡

60.በዚህ ዙሪያ የክልል እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሀላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ በፕሮግራሞቹ የተያዘውን ገንዘብ በእቅድ መሰረት ጥቅም ላይ እየዋለ እንዳልሆነ እና ለዚህም ምክንያቶቹ የአስፈፃሚዎች የአቅም ማነስ፣ የበጀት ቶሎ አለመለቀቅ፣ለአንድ ስራ የሚጠየቁ no objectionኖች እና የሚፈጁት ግዜ ከፍተኛ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

61.ክልሎች ለፕሮግራሞቹ ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን ገንዘብ በእቅዳቸው መሰረት በወቅቱ ባለመጠቀማቸው ለመገንባት በእቅድ የተያዙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ እና ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ መሆን በነበረባቸው ወቅት ጥቅም እንዳያገኙ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በእርዳታ/ብድር የተገኘን ገንዘብ በወቅቱ አለመጠቀም በአበዳሪ/ዕርዳታ ሰጪዎች ዘንድ አሉታዊ እይታን ሊፈጥር ይችላል፡፡

## ክልሎች ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት መሰረት አገልግሎት ስለማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች እና ስለተቆፈሩ ጉድጓዶች መረጃ መያዛቸውን እና በመረጃው ላይ ተመስርተው የመፍትሄ እርምጃ መውሰዳቸውን በተመለከተ

62.ክልሎች ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት መሰረት ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ እና ለምን ያህል ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ፣በክልላቸው ምን ያህል የመጠጥ ውሀ ጉድጓድ እንደተቆፈሩ እና ምን ያህሉ እንደመከኑ መረጃ ሊይዙ እና በመረጃው ላይ ተመስርተው አገልግሎት በማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ

ሊወስዱ፣ የመጠጥ ዉሀ ቁፋሮ የሚካሄድባቸዉ ቦታዎች በቂ ፣ቀጣይነት እና አስተማማኝ የመጠጥ ዉሀ ያላቸዉ ስለመሆኑ ሊያረጋግጡ እንዲሁም ሚኒስተር መ/ቤቱና ክልሎች በከተማዎች/ ወረዳዎች ተገንብተው ካለቁ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ውስጥ 90% ቀጣይነት ያለው የውሀ አቅርቦት እንዲሰጡ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

63.በኦዲቱ ወቅት በታዩት የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የሶማሌ፣የሀረር እና የአማራ ብሄራዊ ክልሎች በየክልላቸው ከሚገኙ ቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት ከ2001-2003 ዓ.ም ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ ፣ለምን ያህል ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ፣ በየክልላቸው ውስጥ ምን ያህል የመጠጥ ውሀ ጉድጓድ እንደተቆፈረ እና ምን ያህሉ እንደመከነ የሚያሳይ የተሟላ መረጃ አላዘጋጁም፡፡

64.በዚህ ዙሪያ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ሀላፊዎች በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚደረገው የዋሽ ቆጠራ /WaSH inventory/ ምላሽ የሚያገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

65.በኦዲቱ ከታዩ ወረዳዎች ውስጥ በጃቢ ጠናን 3፣በሶሬ 5፣ እና በድሬ ጥያራ 7 እንዲሁም በጎንደር ከተማ 3 ተቆፍረው የመከኑ ጉድጓዶች ተገኝተዋል፡፡

66.ክልሎች ከላይ የተጠቀሱትን መረጃዎች አጠናክረው ባለመያዛቸው የተገነቡ የመጠጥ ውሀ ስራዎች መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት መስጠት ላለባቸው ግዜ እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣የተበላሹ የመጠጥ ውሀዎች እንዲጠገኑ ለማቀድ እና መጠገናቸውንም ለመከታተል እንዳይችሉ ከማድረጉም በላይ በአጠቃላይ በክልላቸው ያለውን የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ግንባታ አቅርቦት እና ቀጣይነት ለመከታተል፣ለመቆጣጠር እንዲሁም ድጋፍ ለማድረግ እንቅፋት ሆኗል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

67.በውጪ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፡፡ከክዋኔ ኦዲት ዋናዋና አላማዎች አንዱ በመንግስት የሚስተባበሩ እና በውጪ ድጋፍ/እርዳታ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች በአግባቡ ተፈፃሚ እና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ከዚህ አላማ አንጻር በውጪ ድጋፍ/እርዳታ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም እና ውጤታማነት የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ያሉበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

68.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ውሃ ቢሮዎች ፈንድ በሚሰጡ ባንኮች የግዥ ስርአት እና በLC አከፋፈት ዙሪያ በቂ ስልጠና ባለመስጠቱ እንዲሁም ክልሎች ለወረዳ ውሀ ፅ/ቤቶች በመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታ እና ጥገና ዙሪያ በቂ ስልጠና ባለመስጠታቸው የጨረታ ዶክመንት ዝግጅት፣no objection ሂደት እና የፕሮጀክቶች ግንባታ እንዲጓተቱ ምክንያት መሆኑ፤

69.በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጠናቀረ የኮንትራክተሮች መረጃ አለመኖሩ በቂ አቅም የሌላቸው ኮንትራክተሮች በጨረታ እንዳይሳተፉ ለማድረግ አለመቻሉ፣

70.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀዉ የካፒታል እና የመደበኛ ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በWaSH የመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና አቅርቦት ዙሪያ ያጋጠሙ የግንባታ መዘግየቶችን እና የፋይናንስ አጠቃቀም ዝቅተኝነትን ባለማካተቱ የሪፖርቱ ተጠቃሚ የተሞላ መረጃ እንዳያገኝ መደረጉ፣

71.ክልሎች ለመጠጥ ውሀ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የተመደበላቸውን ገንዘብ በእቅዳቸው መሰረት ባለመጠቀማቸው በእቅድ የተያዙ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ ገደብ እንዳይጠናቀቁ እና ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ መሆን በነበረባቸው ወቅት ጥቅም እንዳያገኙ ማድረጉ፤

72.ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ግዜ ባለመጠናቀቃቸው ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ መሆን በነበረባቸው ወቅት ጥቅም እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ በየግዜው በሚፈጠረው የዋጋ ንረት ምክንያት ፕሮጀክቶቹ መጀመሪያ ከተያዘላቸው በጀት በተጨማሪ እንዲጠይቁ ማድረጉ፤

73.ክልሎች ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ እና ለምን ያህል ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ መረጃ አጠናክረው ባለመያዛቸው የተገነቡ የመጠጥ ውሀ ስራዎች መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት መስጠት ላለባቸው ግዜ እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣የተበላሹ የመጠጥ ውሀዎች እንዲጠገኑ እና መጠገናቸውንም ለመከታተል እንቅፋት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

74.ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ኃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ

75.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል ዉሀ ቢሮ እና ለከተማ ዉሀ ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ፍላጎትን መሰረት አደርጎ ስልጠና ሊሰጥ እና ለክልል ውሀ ቢሮዎች/ከተማ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎቶች የሰጠዉ ስልጠና ያስገኘውን ዉጤት የሚለካበት የአሰራር ሥርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

76.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኮንተራክተሮችን መረጃ አጠናቅሮና በየአመቱ ወቅታዊ አድርጎ በመያዝ በመጠጥ ዉሀ ግንባታ ላይ ከሚሰሩ ኮንትራክተሮች እና አማካሪዎች የተሻለ የስራ አፈጻጸም እና አቅም ያላቸዉን በመለየት የክልል ዉሀ ቢሮዎች/ከተማ ውሀ ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች ጨረታ በሚወዳደሩበት ወቅት ሊጠቀሙበት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና አቅርቦት ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

77.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀዉ የካፒታል እና የመደበኛ ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ በመጠጥ ዉሀ ግንባታ እና አቅርቦት ዙሪያ ያጋጠሙ የግንባታ መዘግየቶችን እና የፋይናንስ አጠቃቀም ከበጀት አመቱ አፈፃፀም ጋር በማነፃፀር የሪፖርቱ ተጠቃሚ የተሞላ መረጃ እንዲያገኝ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ሪፖርቱን የተሟላ ሊያረግ ይገባል።

78.ፈንድ ከሚሰጡ ባንኮች ጋር ተወያይቶ ለአንድ ስራ የሚጠየቁ no objection ኖችን እና የሚፈጁትን ግዜ በመቀነስ፣ለክልል ውሃ ቢሮዎች እና ለከተማ ውሃ ፍሳሽ አገልግሎቶች በ no objection አዘገጃጀት ዙሪያ በቂ እና ተከታታይ ስልጠና በመስጠት ለno objection ምላሽ ያስቀመጠውን የግዜ ገደብ ተግባራዊ ሊያርግ ይገባል፡፡

79.በውጭ እርዳታ እና ብድር የሚደገፉ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ንፁህ ውሃ ለሕብረተሰቡ በታቀደው መልክ እንዲዳረስ በየአመቱ የሚገነቡ ፕሮጀክቶችን በአግባቡ በማቀድ፤ በየደረጃው ካሉ ተግባሪ አካላት ጋር ቅንጅት በመፍጠር እና የተመደበውን ገንዘብ በአግባቡ በመጠቀም ፕሮጀክቶቹ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ሊደረግ ይገባል፡፡

80.ክልሎች ሊገነቡ ያሰቧቸዉን የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸዉ ግዜ እንዲጠናቀቁ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የታሰቡ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲያገለግሉ፤በየበጀት አመቱ ሊገነቡ

ያሰቧቸዉን ፕሮጀክቶች በጥንቃቄ በማቀድ ፤ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት፣ኮንትራክተሮችን እንዲሁም አማካሪዎችን ሲቀጥሩ በሌላ ስራ ያልተያዙ መሆኑን እና ስራውን ለመጨረስ ብቃት እና አቅም እንዳላቸው በሚኒስተር መ/ቤቱ በሚዘጋጀው የኮንትራክተሮች ፕሮፋይል አማካኝነት በማረጋገጥ፣ስራዎች ሲተገበሩ ተገቢዉን ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ የመጠጥ ዉሀ ፅ/ቤቶች ድጋፍ በማድረግ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የተመደበላቸዉን በጀት በእቅዳቸዉ መሰረት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡

81.የክልል ውሃ ቢሮዎች በየክልላቸው የተገነቡ የመጠጥ ውሀ ስራዎች መስጠት ያለባቸውን አገልግሎት መስጠት ላለባቸው ግዜ እየሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣የተበላሹ የመጠጥ ውሀዎች በወቅቱ እንዲጠገኑ እና መጠገናቸውንም ለመከታተል ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በየጊዜው በሚመጡ ሪፖርቶች ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ እና ለምን ያህል ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ፣በክልላቸው ምን ያህል የመጠጥ ውሀ ጉድጓድ እንደተቆፈሩ እና ምን ያህሉ እንደመከኑ የሚያሳይ መረጃ አጠናቅረው ሊይዙ ይገባል፡፡

# አባሪ 1

## የመመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች(evaluative criteria) |
|---|---|
| 1 .ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በክልል፣ከተማዎች እና ወረዳዎች የሚከናወኑ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ መጠጥ ዉሀ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ዉጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ የሚያስችል እቅድ ማቀዱን፣ መከታተሉን፣ መቆጣጠሩን እና ማስተባበሩን ማረጋገጥ። | 1.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልል፣ለዞን እና ወረዳ የውሀ ቢሮ ሰራተኞች በመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ግንባታ፣የግገርና ጨረታ ሰነድ አዘገጃጀት ፣በግገር አፈፃጸም ፣በፋይናንሻል አስተዳደር እና በክንውን ሪፖርት አቀራረብ ዙሪያ ፋላጎትን መሰረት አድርጎ ስልጠና እና ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| 1.1ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ ፕሮግራሞች/ ፕሮጀክቶችን ለሚተገብሩ ክልሎች ፣ ከተማዎች እና ወረዳዎች ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ እንዲወጡ በስልጠና ፣በቴክኒክ ድጋፍ እና በእቅድ አፈፃጸም ዙሪያ በቂ እገዛ ማድረጉን ማረጋገጥ። | 2. ስልጠናዎችያስገኙት ጠቀሜታ በየጊዜው (Training Impact Assessment) መለካት ይኖርበታል፡፡ |
| | 3.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ግንባታ እና አቅርቦትን በተመለከተ የስራቴጂክ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 4.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የስራቴጂክ እቅድ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን በየአመቱ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 5.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ግንባታና አቅርቦትን በተመለከተ አመታዊ እቅድ እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት ማቅረብ ይገባዋል፡፡ |
| 1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጪ በሚገኝ ብድርና ዕርዳታ በክልል ከተማ እና ወረዳዎች የሚተገበሩ እና በፌዴራል ደረጃ የሚስተባበሩ የንፁህ ውሃ ኘደክቶች ግንባታ በታቀደላቸው የገንዘብ እና የጊዜ ደረጃ መፈፀማቸውን መከታተሉን እና መቆጣጠሩን ማረጋገጥ፣ | 6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው አመታዊ የእቅድ ክንውን ሪፖርት .ውስጥ በአፈፃፀም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን ሊያካትት ይገባል፡፡ |
| | 7.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወረዳ ውሀ ፅ/ቤት የውሀ ተቋማትን የሚያስተዳድርበት መመሪያ(guideline )ሊያዘጋጅ ይገባል |
| | 8.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውክልና ለሰጣቸው ክልሎች የ"no objection" ምላሽ አሰጣጥ መመሪያ ሊያዘጋጅ እና ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 9.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የ "no objection" መልስ የሚሰጥበት የግዜ ገድብ ሊያዘጋጅ ይገባል ፡፡ |
| | 10.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልል ከተሞች/ወረዳዎች የሚከናወኑ የመጠጥ ውሀ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በክልሎች በሚጠናከር ሪፖርት እና በአካል ጉብኝት በማድረግ መከታተል፣መቆጣጠር እና ድጋፍ መስጠት ይገባል፡፡ |
| | 11.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጪ እርዳታ/ድጋፍ የሚሰሩ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ሂሳብ አፈፃጸምን በየ 4ወሩ ከክልሎች በሚላክ ሪፖርት መሰረት ሊከታተል እና ሊቆጣጠር ይገባል |
| 1.3 በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ እና ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ድጋፍ የንፁሀ መጠጥ ውሀ ፕሮግራሞችን /ፕሮጀክቶች ተግባራዊ | 12.በውጪ እርዳታ/ብድር የሚደገፉ እና በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ግንባታዎች በተያዘላቸው የግዜ እና የገንዘብ ገደብ ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡ |
| | 13.በክልሎች ከተሞችና ወረዳዎች የሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች በሚኒስተር መ/ቤቱ የታደሰ ፍቃድ በተሰጣቸው ኮንትራክተሮች ሊገነቡ ይገባል፡፡ |

| | |
|---|---|
| የሚያደርጉ ክልሎች በስራቸው የሚገኙትን ፕሮጀክቶችን ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጸሙ እና ግንባታዎች በታቀደላቸዉ የገንዘብ እና ግዜ ደረጃ መፈጸማቸዉን ማረጋገጥ። | |
| | 14.በክልሎች የሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች በቅድሚያ የጥናት እና የዲዛይን ስራ የተጠናቀቀላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 15.በክልሎች የሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ጥናት እና ዲዛይን በተመሳሳይ አካል ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 16.በክልሎች ለሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች የተሰሩ የጥናት እና የዲዛይን ዶክመንቶች እንደ ፕሮጀክቶቹ አይነት የሚገመገሙበት የግዜ ገደብ መስፈርት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 17. ክልሎች በከተማዎች እና ወረዳዎች የሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ወጪ እና የግንባታ ደረጃቸው(physical progress) የተጣጣመ መሆኑን በአማካሪዎች በሚቀርብ የክፍያ ማረጋገጫ/payment certificate/ ሊያረጋግጥ ይገባል |
| | 18.ክልሎች በ channel 1 ወይም channel 2 የሚለቀቅላቸውን የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ፈንድ/ገንዘብን በእቅዳቸውና በፕሮጀክት ስምምነት ሰነድ መሰረት ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ |
| | 19 በውጪ እርዳታ/ብድር የሚደገፉ እና በውሀ ልማት ፈንድ ፅ/ቤት በኩል የሚስተባበሩ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የግዜ እና የገንዘብ በጀት ሊጠናቀቁ ይገባል፡፡ |
| | 20.ክልሎች በየበጀት አመቱ ሊገነቡ ላቀዱትእና እየተገነቡ ላሉ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸውን የእቃ እና የአገልግሎት ግዢ ፍላጎት እቅድ ሊያዘጋጁ እና ለሚኒስተር መ/ቤቱ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡ |
| 1.4በፌደራል ደረጃ የሚስተባበሩ እና ከውጪ በሚገኝ ብድርና እርዳታ ድጋፍ የንፁህ መጠጥ ውሀ ፕሮግራሞችን /ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ የሚያደርጉ ክልሎች ፕሮጀክቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ቀጣይነት ያለው አቅርቦት/አገልግሎት እንዲሰጡ መከታተላቸውን እና መቆጣጠራቸውን ማረጋገጥ። | 21.ክልሎች ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት ተገንብተው ያለቁ እና አገልግሎት የማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶችን አገልግሎት ያቆሙበትን ምክንያት፣አገልግሎት ያቆሙበትን ጊዜ እና ለምን ያህሉ ግዜ አገልግሎት እንደሰጡ መረጃ አጠናክሮ ሊይዙ ይገባል፡፡ |
| | 22.ክልሎች ከቀበሌ፣ወረዳ እና ዞኖች በሚመጣ ሪፖርት ላይ ተመስርተው አገልግሎት በማይሰጡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡ |
| | 23.የክልል ውሀ ቢሮዎች የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ሽፋንን ለማሳደግ እና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ የግንዛቤ መፍጠር ስራ ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 24 የክልል ውሀ ቢሮዎች በመጠጥ ውሀ ፕጀክቶች ግንባታ፣የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ተገንብተው የተበላሹ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች እድሳት እና ሌሎች ከመጠጥ ውሀ ግንባታ ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 25.ክልሎች በከተማ የተገነቡ የመጠጥ ዉሀ ፕሮጀክቶች በቀን ለ6 ሰአት በሳምንት ለ5ቀናት አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን የሚረጋግጡበት ስርአት ሊዘረጉ ይገባል። |
| | 26.ክልሎች የመጠጥ ዉሀ ቁፋሮ የሚካሄድባቸዉ ቦታዎች በቂ ፣ቀጣይነት እና አስተማማኝ የመጠጥ ዉሀ ያላቸዉ ስለመሆኑ በበቂ ጥናት ሊያረጋግጡ ይገባል። |

| | |
|---|---|
| 2.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት/ፕሮግራሞችን ተፈፃሚ ከሚያደርጉ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን እና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥና የፍላጎት ጥናት ስርአት መዘርጋቱን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ። | 27.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል፣ዞን፣ወረዳ ውሀ ቢሮዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በየ6 ወሩ ስለ መጠጥ ውሀ ፕሮጀክት አፈፃፀም እና ስለአጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም መወሰድ ስላለባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ውይይት የሚካሄድበት የመወያያ መድረክ ሊፈጥር ይገባል፤፤ |
| | 28.ሚኒስቴር መ/ቤቱና ክልሎች በከተማዎች እንዲሁም ወረዳዎች ተገንብተው ካለቁ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ውስጥ ቢያንስ 90% ቀጣይነት ያለው የውሀ አቅርቦት እንዲሰጡ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 29.ክልሎች በየበጀት አመቱ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክት ግንባታ ጥናት በሚያዘጋጁ ወቅት የቀበሌ፣የወረዳ የዞን እና የከተሞች ፍላጎት እና ጥያቄን ምላሽ የሚሰጥ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 30.ሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ክልሎች በከተማዎች/ወረዳዎች አዲስ የሚገነቡ የመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ለምን ያህል ጊዜ (project time) እና ህዝብ አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በጥናት ውስጥ ሊያካትቱ ይገባል፡፡ |
| | 31.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከውጭ ብድር እና እርዳታ ለመጠጥ ዉሀ አቅርቦት የሚያገኘውን ፈንድ በፌደሬሽን ምክር ቤ/ት ቀመር መሰረት ለክልሎች ሊያከፋፍል ይገባል ፡፡ |
| | 32.ለመጠጥ ውሀ ፕሮጀክቶች ፈንድ የሚለቀቅላቸው ክልሎች ስለፈንዱ አጠቃቀም፣ እየተገነቡ ስላሉ ፕሮጀክቶች ክንውን እንዲሁም ስለአጋጠሚቸው ችግሮች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በየ3 ወሩ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ |
| | 33.ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎች ጋር በመተባበር በየ6 ወሩ ስለፕሮጀክቶች አፈፃጸም እና ፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት ሊያዘጋጅ እና ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሊልክ ይገባል፡፡ |